## በጤና አገልግሎት አስተርጓሚ ኣለመጠቀምዎ አቤቱታ ኣልዎት?

Fylkeslegen / **የዞን ሃኪም በሚኖሩበት ዞን** (www.helsetilsynet.no)
Pasient- og brukerombudet / **የበሽተኛና የተጠቃሚ ተጣባቂ በሚኖሩበት ዞን** (www.pasientogbrukerombudet.no)
Sivilombudsmannen **የሲቪላውያን ተጣባቂ (የህዝብ ብሶት ሰሚ) ቴሌ**: 22 82 85 00 **በኣረንጓዴ ቁጥር**: 800 800 39
Likestillings- og diskrimineringsombudet / **የእኩልነትና የኣድልዎ ተጣባቂ (ማግለል) ቴሌ**: 24 05 59 50
Organisasjon Mot Offentlig Discriminering (OMOD) / **በህዝብ ባለስልጣን ለሚደረግ ኣድልዎ ተጣባቂ ማሕበር ቴሌ**: 22 20 87 37 (www.omod.no)

## ስለ መብትዎ በሚመለከት ጥያቄ ኣልዎት?

Pasient- og brukerombudet / **የበሽተኛና የተጠቃሚ ተጣባቂ በሚኖሩበት ዞን**
(www.pasientogbrukerombudet.no)
Organisasjon Mot Offentlig Discriminering (OMOD) / **በህዝብ ባለስልጣን ለሚደረግ ኣድልዎ ተጣባቂ ማሕበር** (www.omod.no) **ቴሌ**: 22 20 87 37

## የአስተርጓሚ ችሎታና ብቃት በሚመለከት ኣቤቱታ ኣልዎት?

**ኣቤቱታዎ ሕክምና በሚከታተሉበት ድርጅት ማቅረብ ይቻላሉ።**

**ስለ የበሽተኞች መብትና ስለ የጤና ባለሞያዎች ግዴታ የሚመለከት ሕግ**
**የበሽተኞች መብት ሕግ** (Pasientrettighetsloven)
**የጤና ባለሞያዎች ሕግ** (Helsepersonalloven)

**ይህ ኣጭር ጽሑፍ ከሃያ ቋንቋዎች በላይ ተተረጉሞ ይገኛል።**
www.nakmi.no **በሚባል የኢንተርኔት ሳይት ገብቶ ዳውንሎድ ማድረግና ማንበብ ይቻላል።**
www.helsedirektoratet.no



# በሽተኛና አስተርጓሚ

## በጤና ኣገልግሎት ስለ አስተርጓሚ የሚመለከት ጽሑፍ

NAKMI
Helsedirektoratet

## በሽተኞችና መተርጐም

- የጤንነትዎን ሁኔታና የሚደረግልዎትን ሕክምና በሚመለከት እርስዎ በሚግባቡበት ቋንቋ መረጃ ይሰጥዎታል።
- የጤና አገልግሎት አስተርጓሚ የማቅረብ ግዴታና ሃላፊነት አለበት።
- የትርጉም አገልግሎት ለበሽተኞች በነጻ ይሰጣል።
- ወደ ጤና አገልግሎት በመደወል አስተርጓሚ እንዲያቀርብልዎት መጠየቅ ይችላሉ።
- የኖርዌጅያን ቋንቋ በየቀኑ የሚናገሩ ቢሆኑም አስተርጓሚ ማግኘት መብት አለዎት። ይህም በተለይ ስለ አደገኛ፣ ስር የሰደደ በሽታዎችና ስነ ኣእምሮኣዊ በሽታ ንግግር በሚያደርጉበት ይጠቅምዎታል።
- ብቃት ያለው አስተርጓሚ ብቻ መጠቀም ኣለብዎት።
- ልጆችን እንደ አስተርጓሚ መጠቀም የለብዎትም።
- የጤና ባለሞያ ደህንነትዎን በተጠበቀ መንገድ የጤና እርዳታ መስጠት ግዴታ አለበት። አስተርጓሚ አልፈልግም ካሉ፣ ባለመግባባት የተነሳ በጤንነትዎ ላይ ኣሉታዊ ውጤት እንደሚያስከትል ይነገርዎታል።
- አስተርጓሚው እርስዎ ባሉበት ቦታ ሳይገኝ፣ ማስተርጐሙ በቴሌፎን ማድረግ እንደ አንድ ጥሩ አማራጭ ሊሆን ይችላል ።
- በቀጠሮዎ መገኘት የማይችሉ ከሆኑ 24 ሰዓት ኣስቀድመው፡ ቀጠሮውን መሰረዝ ኣለብዎት። አለበለዚያ ከሓኪም ያደረጉትን ቀጠሮ መክፈል ግዴታ ይኖርብዎታል።

## እንዴት ኣድርገው በአስተርጓሚ ኣማካኝነት የሚደረግ ንግግር ይበልጥ መጠቀም ይችላሉ?

- እርስዎ የሚናገሩትን ቋንቋ በትክክል ኣድርገው ለጤና ባለሙያዎች ይንገርዋቸው። ከአንድ ቤተሰብ ወደ ቀጠሮው የሚቀርቡ ኣባላት ብዙ ከሆኑ ከሁሉንም መግባባት የሚችል አስተርጓሚ መጠየቅ ይበጃል።
- በተሰጥዎት ቀጠሮ በሰዓቱ መገኘት ኣለብዎት።
- በሚመረመሩበት ግዜ ምን መናገር እንዳለብዎት አስበውበት ይቆዩ።
- አጫጭር አረፍተ ነገሮች ይጠቀሙ፡ ባንዴ ብዙ አይናገሩ። እንዲህ ካደረጉ  አስተርጓሚው እርስዎ የሚሉትን በትክክል ለመተርጐም ይቀለዋል።

## አስተርጓሚ ምንድን ነው፡ የአስተርጓሚ ስራስ ምንድነው?

- አንድ ብቁ አስተርጓሚ የማስተርጐም ትምህርት የተማረና የማስተርጐም ልምድ ያለው ሰው ነው።
- አንድ አስተርጓሚ፡ መናገር ሲጀምር፡ የአስተርጓሚ ስርዓቶችን በሁለቱም ቋንቋዎች ይገልጻል።
- አንድ አስተርጓሚ በንንግሩ ሂደት ገለልተኛ መሆን አለበት።
- አንድ አስተርጓሚ ምስጢር የመጠበቅ ግዴታ ኣለበት። ምስጢር መጣስ በሕግ ያስቀጣል።
- አንድ አስተርጓሚ የተባለውን ሁሉ ይተረጉማል። ነገር ግን ምክር መስጠት ወይንም የራሱ አስተያየቶችን ማበርከት ኣይችልም።
- አንድ አስተርጓሚ ስራው ማስተርጐም ብቻ ነው፡ ከዚህም አልፎ የበሽተኛው ሆነ የጤና ባለሙያዎች ስራ መስራት አይችልም።
- አስተርጓሚው ሲተረጉም ማቋረጥ ኣይገባም፡ ሆኖም ባለጉዳዮች የተናገሩትን ለመተርጎም ጊዜ ማግኘት ኣለበት።
- ሁሉም ጥያቄዎች ለተርጓሚው ሳይሆን ለጤና ባለሞያው መቅረብ አለባቸው።